# መኢሶንና ኢሕአፓ በአብዮቱ ወቅት ምን ሠርተው አለፉ ?

ይኼንን ጥያቄ በአግባቡ መመለሱ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የነበረው ልዩነት አንዳዶቹ እንደሚሉት ጥቃቅን የሚባል እንዳልነበረና ፣ ይልቁንም በአብዮተኞችና በፀረ - አብዮተኞች መካከል የነበረ ልዩነት መሆኑን በግልጽ ያሳያል ብዬ አምናለሁ ። በኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት ተካሒዶ እንደነበር በመኢሶንም ሆነ በኢሕአፓ በኩል ሥምምነት ያለ ይመስለኛል ። ይኼን አብዮት የመራው ደግሞ የመንግሥት ሥልጣን ጨብጦ የነበረው ወታደራዊው መንግሥት እንደሆነ ግልጽ ነው ። ምክኒያቱም የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው አካል ፍላጎቱን በሌሎች ላይ ማስፈን ይችላልና ። በዚህን ወቅት ግን መኢሶንና ኢሕአፓ በአንድ ጎራ ተሰልፈው አልተገኙም ። መኢሶን በአብዮቱ ጎራ ሲሰለፍ ፣ ኢሕአፓ ግን ጎራው ከፀረ-አብዮተኞች ጋር ሆኖ አረፈው ። ኢሕአፓ ፀረ-አብዮተኛ ብቻ ሳይሆን የሆነው ፣ ለአገር ጠላቶችም የአምስተኛ ረድፈኝነት ሚናን ተጫውቷል ። **አምስተኛ ረድፈኛ ማለት ፤ አንድ በሚስጥር የተደራጀ ቡድን ሲሆን ፣ ለጠላት በመወገን የራሱን ሕዝብ ጥቅም በማንኛውም መልኩ ከመሀል ሆኖ የሚቦረቡር ማለት ነው ።** እንደዚህ ዐይነቱ ጠላት ደግሞ ከለየለት የውጭ ጠላት የበለጠ አደገኛ ነው ። ለዚህም ነው ፤" **ፈጣሪዬ እኔ ከጠላቶቼ እራሴን ስከላከል አንተ ከወዳጅ ጠላት ጠብቀኝ** " ተብሎ የሚፀለየው ። ይኼንን በአገር ላይ የተሸረበ ደባ የኢሕአፓ አባሎች በሙሉ ያውቁ ነበር ወይ ተብሎ ቢጠየቅ ፣ መልሱ እንኳን ያኔና አሁንም ድረስ ቢሆን አብዛኞቹ አያውቁም ነው የሚሆነው ። ነገር ግን እነ ብርሃነ መስቀልንና ጌታቸው ማሩን ከአመራር ያስወገደው አፍቃሪ ሻዐቢያ የአመራር ወገን ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ። እንደውም በ1969 ዓ/ም አጋማሽ ላይ በአንደኛው የሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ ጉባዔ ኢሕአፓን ወክለው ለተገኙት ልዑካን ፣ የደቡብ የመን መንግሥት የፀጥታ ኃላፊና የኮሚኒስት ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆነው ግለሰብ ፡ " ደርግ በቅርቡ የግንባር ጥሪ ስለሚያቀርብ ጥሪውን ተቀብለው መሳተፍ እንዳለባቸው ሓሳብ ካቀረበ በኂላ ፣ የኢሳያስ አፈወርቂ ድርጅት ኢትዮጵያን ለመበታተን ቆርጦ የተነሳ እንደሆነና ከእሱ ጋር መተባበር እንደሌለባቸውም ያሳስባቸዋል " ብሎ (ጸሐየ) እንደነገረው አስማማው ኃይሉ 2003 ዓ/ም ቅጽ አንድ " ኢሕአሠ " (ከ1964-70ዓ/ም) ብሎ ባሳተመው መጸሐፉ ገጽ 226 ላይ ያወሳናል ። የኢሕአፓ አመራር ግን ለምክሩ ጆሮ ባለመስጠት እስከመጨረሻው ድረስ በጥፋት ጎዳናው ዘልቆበታል ።

መኢሶን የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው ደርግ አብዮቱን መምራት ሲጀምር ፣ የአቋም ለውጥ በማድረግ አብዮቱን በመምራት ላይ ለነበረው ወታደራዊ መንግሥት ሂሳዊ ድጋፍ መስጠት ጀመረ ። በኂላም ላይ የጠራ የፖለቲካ መመሪያ ላልነበረው ወታደራዊ መንግሥት ፣ **የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም** ነድፎ በደርጉ ተቀባይነትን ካገኘ በኂላና ፣ ለተራማጆች አመቺ የትግል መድረክን ከፈጠረ በኂላ ፤

1. የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት እዲቋቋም በማድረግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለነቃ ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ የሕዝብ ትግል እንዲዘጋጅ (ምንም እንኳን በሻዐቢያ አስተባባሪነት የሚንቀሳቀሰው የኢሕአፓ ገዳይ ቡድን ቢያስቸግረውም) በገጠርና በከተማ ተንቀሳቅሷል ።
2. የፖለቲካ ትምህርት ቤት እንዲቋቋም በማድረግና በማስተማር ሠፊው ሕዝብ ንቃተ - ህሊናው እንዲዳብር አድርጓል ።

3. በአዲስ አበባና በኢሉ አባቦራ (መቱ) ላይ በርካሽ ዋጋ የማርክሲስት ርኡተ-ዓለምን ለማስፋፋት የሚረዱ መጻሐፍቶችን መሸጫ መደብሮችን ከፍቶ ወጣቱ ንቃተ ሕሊናውን እንዲያዳብር በማድረግ አስተዋፆ አድርጓል ፡፡
4. በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የአብዮት መድረክ የሚባል አምድ ተከፍቶ (ደርግ ክርክሩ እንዳይካሔድ እስከ ከለከለበት ጊዜ ድረስ) የፖለቲካ ውይይቶች እንዲደረጉ አድርጓል ፡፡ ይኼም መድረክ መኢሶንን የፖለቲካ መስመሩን በሕዝብ ውስጥ በሠፊው እንዲያሰራጭ ረድቶት ነበር ፡፡ ለመድረኩም መቀጠል መኢሶን ቢከራከርም ወታደራዊው መንግሥት አሻፈረኝ በማለቱ ክርክሩ ሊቋረጥ ችሏል ፡፡
5. በየመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ውስጥ በሣምንት ሁለት ቀን በፈቃደኝነት የፖለቲካ ውይይት እንዲካሔድ አድርጓል ፡፡ በውይይቱ መካፈል የማይፈልጉ ሠራተኞች ግን መደበኛ ሥራቸውን ማከናወን ይጠበቅባቸው ነበር ፡፡ (መኢሶን ከሕብረቱ ጥሎ ከወጣ በኋላ ፣ ውይይቱ የሚካሔደው በፈቃደኝነት ሳይሆን በግዳጅ ሆኖ አግኝቸዋለሁ ፡፡)

ከፍ ብሎ የተመለከታችሁት የኔ ምስክርነት ሲሆን ፣ በወቅቱ የሠደድ አባል የነበሩትና " **ነበር** " የሚለውን መጻሐፍ የደረሱት ደራሲ ገሥጥ ተጫኔ ገጽ 273 እና 275 ላይ ስለመኢሶን የሚከተለውን ምሥክርነት ሠጥተው እናገኘዋለን ፡፡

*ሀ - "በመጨረሻም ወገን መስሎ ደርግ ሲስቅ እየሳቀ ፤ ደርግ ሲያኮርፍ እየበረገገ የቆየው መኢሶን ሁሉን ነገር ትቶ ሔደ ፡፡* ***ከእንግዲህ የጓድ ሊቀ መንበር አመራርን የሚፈታተን ማነው የሚል ጥያቄ መጣብኝ*** *" በማለት መኢሶን በራሱ ጎራ ውስጥ ከመንግሥቱ ኃይለማርያምም ቡድን ጋር በነበረው ልዩነት ላይ ይታገል እንደነበር ጠቆም ያደርጋሉ ፡፡*

*ለ - " መኢሶን በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ / ቤት መቋቋም ሰበብ ከደርግ ጋር ከተወዳጀበት ጊዜ አንስቶ ከሞላ ጎደል ለሁለት ዓመት ያህል ለአብዮቱ ሂደት መቃናት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉን አውቃለሁ ፡፡ ለምሣሌ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እንዲወጣ ፤ የአብዮቱ ወገኖች ነቅተው በየፈርጃቸው ተደራጅተውና ታጥቀው እንዲታገሉ ፣ የኤርትራ ጉዳይ በውይይት መድረክ እንዲፈታ ጥረት ካደረገባቸው ብሔራዊና አብዮታዊ ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደነበሩ አስታውሳለሁ ፡፡ " በማለት ይመሰክራሉ ፡፡ የኢሕአፓ አባል የነበሩት አቶ ታክሎ ተሾመ ደግሞ "የደም ዘመን" ብለው ግንቦት 2003 ዓ/ም ባሳተሙት መጻሐፋቸው ገጽ 246 ላይ ፤ "* በ1966 ዓ.ም አብዮት እንደፈነዳ በአገር ውስጥ የተማሪውን ንቃተ-ህሊና ለማዳበር ከዚህ በፊት በአገራችን ያልነበሩ የነፃነት ትግል የሚያወሱና ለነፃነት ለሚደረገው ትግል ቅድመ ዝግጅት የሚሆኑ መጽሀፍቶችን ከቻይና በማስገባትና የኮሚኒዝምንና የሶሻሊዝምን ትርጉም ሁሉም እንዲረዳው በማድረጋቸው ማህበረሰቡን አነቃቅተው አደራጅተዋል ፡፡ በተለይ የሰፊው ህዝብ ድምፅ በተሰኘ መጽሄት ልዩ ልዩ መጣጥፎችን እያወጡ የወጣቱን ንቃት ከፍ አድርገውታል ፡፡ የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም የመሬት አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረጋቸውም አይዘነጋም ፡፡ በከተማ ወዝአደሩን ፤ ወጣቱንና ሴቶችን በማደራጀትና በማንቃት ያሳሰለሰ ጥረት ማድረጋቸውና በሳል የድርጅት አባላትም እንደነበሩ እውነት ነው ፡፡ " *ሲሉ ስለ መኢሶን አስተዋፆ ይመሰክራሉ ፡፡*

*በሌላ በኩል ደግሞ ኢሕአፓስ በአብዮቱ ወቅት ምን ሠርቶ አለፈ ብለን ብንጠይቅ የሚከተለውን እናገኛለን ፡፡ ኢሕአፓ ከኤርትራ "ነፃ-አውጭ" ግንባር ጋር በገባው ወታደራዊ ውል መሠረት (በነገራችን ላይ የኢሕአፓ አመራር እስካሁን ድረስ ከሱማሌ መንግሥትና ከኤርትራ ግንባሮች ጋር የተዋዋለውን ውል ሙሉ ይዘት ለአባሎቹም ሆነ ወይም ደግሞ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እስካሁን ድረስ ይፋ*

*አላደረገም) እጅና ጓንት በመሆን በኢትዮጵያ ከተማዎችና ገጠሮች በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ጦርነትን ከፈተ ። በዚሁም ፤*

1. *ከሻዐቢያ ጋር በመሆን ያገር መከላከያ ሚሥጥርን አሳልፎ ከመስጠቱ በተጨማሪም ተባብሮ የአገር መከላከያ ኃይልን ወግቷል ። ሠራዊቱ ጦሩን እየከዳ ለሻዐቢያ እጁን እንዲሠጥ በማድረግ ወደ ሁለት ሻለቃ ጦር ማስፈጀቱን እስካሁን ይፋ አድርጓል ።*
2. *የማይረባ የገንዘብና የመሣሪያ እርዳታ ሰጠኝ ለሚለውም የሱማሌ መንግሥት በመወገን የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አልተሳካም እንጂ እንዳይዋጋ ቅስቀሳ አድርጎ ነበር ።*
3. *ባላባቱንና በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ጊዜ ሹማምንት የነበሩትን የሕብረተ-ሰብ ክፍል በማደራጀት የኢትዮጵያን ደሃ ገበሬ በሠሜን ኢትዮጵያ ወግቷል ።*
4. *የኢሕአፓ አመራር ለሥሙ ማርክሲስት ነኝ ይበል እንጂ ማርክሲዝም ሌኒንዝም በአገሪቱ እንዳይስፋፋ የፖለቲካ ትምህርት ቤቱን ፣ ጊዜን ጠብቆ በሚፈነዳ ቦምብ (TIME BOMB) ተጠቅመው ሲያቃጥሉ ፣ መምህራኖቹን ሲገድሉና ሲያቆስሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአዲስ አበባ ተከፍቶ ከነበረው መጻሐፍት ቤት ወጣቱ የማርክሲዝምን መጻሐፍት እንዳይገዛ ለማድረግ በድንጋይ መደብደብ ጀመሩ ። በመቱ ከተማ የተከፈተውን መጻሐፍት ቤት ደግሞ በእሣት አቃጠሉት ። እኛ እንኳን መጻሐፍቶቹን በርካሽ ነበር የምንሸጣቸው ፣ ምነው በብዛት ገዝተው አባሎቻቸውን ከመዝሙር ፋንታ ማርክሲዝምን እንዲያጠኑ ቢያደርጓቸው ። እኔ የማይገባኝ ነገር ፣ ጠባቸው ከመኢሶን ጋር ነበር ወይንስ ከማርክሲዝም ጋር ?*
5. *የኤርትራ ግንባርን በተመለከተ መኢሶን ገና እንደ ተመሠረተ በተማሪው ማኅበር ሥም ፤ ነሐሴ 1960 ዓ/ም በይጎዝላቪያ ፤ ዛግሬብ ከተማ ውስጥ ተደርጎ የነበረው የአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር (የአኢተማ) 8ኛ ጉባኤ የወሰደው አቋም ፤ “ የግንባሩ (የኤርትራ) አመራር የሚከተለው ፖለቲካ የኤርትራን ሠራተኛና የገበሬ ጥቅምና ፍላጎት የማያረካ ፤ የታጋዩን ሕዝብ ድል ለመሻማት የታቀደ ፖለቲካ መሆኑን በመገንዘብ ፤ በጥብቅ ይኮንነዋል ። … የኤርትራን ሕዝብ ትክክለኛ ተጋድሎ ይደግፋል ። “ ብሎ በግንባሩ ላይ አቋም ወስዶ እንደነበር አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ ብሎ በሰየመው መጻሐፉ ገጽ 21 ላይ ይገልጸዋል ። እነዚህ ኢትዮጵያዊ ታጋዮች የግንባሩን መሠሪ አካሔድ ቀድመው የተረዱ በመሆናቸው የተነሣ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ ላይ በማንኛውም መንገድ መገለል ነበረባቸው ። ለዚሁም መሣሪያ ሆኖ የተገኘው የኢሕአፓ አመራር ሆኖ አረፈው ። በዚሁም መሠረት በቅድሚያ በ1967 ዓ/ም ማለትም መኢሶን ከደርግ ጋር የፖለቲካ ሕብረት ከመመስረቱ በፊት ግድያ ኢላማ ውስጥ እንዲገባ ተደረገ ። ሆኖም ግን አንዳንድ የኢሕአፓ አባላት የመኢሶን አባላትን መገደል ስለተቃወሙ ግድያው እስከ መስከረም 1969 ዓ/ም ድረስ ሊዘገይ ቻለ ። የኢሕአፓ አመራር ይኼንን ሁሉ ወንጀል ሲያከናውን የነበረው ደጃችውቤ ሠፈር ከሚገኘው የሻዐቢያ ቡድን ጋር (ከነኀይቶም ለባሲ ጋር) በማቀነባበር ነበር ።*
6. *በመጨረሻም አንዳንድ የኢሕአፓ አባሎች ኢትዮጵያዊ አጀንዳ አለማከናወናቸውን በመገንዘባቸው ፣ በኢሕአፓ አመራር ላይ ጥያቄዎችን ማንሣት ሲጀምሩ ፣ ሕይወት ተፈራ “ TOWER IN THE SKY “ ብላ በሰየመችው መጻሐፏ ላይ የምታነሣቸው እንደነ ጌታቸው ማሩ ፣ ኢዮብ ፣ እንድሪያስ ፣ በክሪና ጌታቸው አሰፋን የመሳሰሉትን እያሳደዱ መግደል ጀመሩ ። በመጨረሻም ኢሕአፓ በገበሬው ደም በመጨማለቁ የተነሣ በሠሜን ኢትዮጵያ መጠጊያ አጥቶ ወደ ሱዳን መፍለስ ተገደደ ። ከዚያ በኋላ ማን እንዳዘጋጀው ባልታወቀ መንገድ ፣ ፀረ-ኮሚኒስት ነኝ የሚለው የአሜሪካን መንግሥት “ የእኛን*

*ኮሚኒስቶች “ አውሮፕላን ካርቱም ድረስ አቅርቦ አንገዞ ወሰዳቸው ። ጥያቄው ፣ ኢሕአፓ ለአሜሪካን መንግሥት በወቅቱ ምን ውለታ ውሎ ይሆን ? የሚለው ነው ። እንግዲህ ታሪካችን ባጭሩ ይኼንን ይመስላል ። ታዲያ ምሁሮቻችን በመኢሶንና በኢሕአፓ መካከል ለግጭት የሚያበቃ ልዩነት አልነበረም ሲሉ ይገርመኛል ። ወይ ዕውቀታቸው ጥራት የለውም ፣ አለበለዚያ ደግሞ ሕዝቡ በተለይ ወጣቱ ትውልድ በወቅቱ የተከናወነውን ነገር እንዳያውቅ አውቀው ያድበሰብሱበታል ። ይኼ ደግሞ አገሪቱን ለሌላ ዙር ችግር ይዳርጋታል የሚል ስጋት አለኝ ። ምክኒያቱም ሻዐቢያም ሆነ የሱማሌ መንግሥት አሁንም የኢትዮጵያ በጎ አሣቢዎች ባለመሆናቸው አሁንም የአገራቸውን ጥቅም ለይተው ያላወቁትን ወገኖቻችንን በድጋሚ ሊያጠምዷቸው ይችላሉ ። ለአሁኑ በዚሁ ላብቃ ።*

*መርዕድ ከበደ*

ሎሚ መዕሄት ቅፅ 2 ቁጥር 75